# የትግራይ ሕዝብ ነጻ-አውጭ
# ግንባር አወጣጡ ከአገባቡ አንጻር



በዘውገ ፋንታ

ሰያትል 2017

*መግቢያ*

የዚህ ጽሑፍ አላማ፣ ስለ ሀገር ወቅታዊ ጉዳይና የወደፊት ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልክ ለማቅረብ ነው። የወቅቱ ቀውስ በሚያስከትለውና ወደፊት ሊሆን በሚችለው ጥሩ ወይም መጥፎ ሁኔታ ላይ ትኩረት ይደረጋል። የወያኔ አገዛዝ እያከተመ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የታሪክ ታላቅነቱ ለዓለም ለማሳየት የሚወስደው ታሪካዊ ምግባር አለ። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ለዚህ በጎ ውጤት ለራሱ ሲል ተባባሪ ይሆናል የሚል ግምትም አለ። የወያኔ ፍላጎት ይህ ካልሆነ፣ ይህ ጽሑፍ በወያኔ እና ተደላቢ ሆኖ በሚታየው ሙሉ አካሉ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ከፋ ውጥንቅጥ አነጻጽሮ ለመግለጽ ይሞከራል። ከዚህ በተጨማሪ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሰረታዊ ለውጥ ለማድረግ ለሚወስደው እርምጃ፣ ከወያኔ ተጨማሪ ሌላ ተቀናቃኝ የውጭ ኃይል እንደ አለፈው ሰፊ ሚና ለመጫወት በስተጀርባ ሰፍሮ የሚገኝ ይኖራል። ኢትዮጵያ ጓዳ የላትም። የውጩ ኃይል የተለመደ ሚናውን ለማካሄድ አሸብሽቦ ከሆነ፣ በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፋለመው እንደሚሆን ወቅቱ የሚመሰክረው ጉዳይ ነው። ይህን ጉዳይ ተተንትኖ ይገልጻል።




የወያኔ አመጣጥ የወያኔ አገዛዝ ፍጻሜ ፍጹም ሰላማዊ እንዲሆን ምኞቱና ፍላጎቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የመላው ዓለም ሕዝብ ጭምር ጭምር እንደሆነ ይታወቃል። ለውጥ በሰላም እንዲመጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኞቱና ፍላጎቱ ብቻ ሳይሆን እስከ አሁን ከንፈሩን መጦ በትግሥት የጠበቀው ጊዜ ስለሆነ፣ በራሱ ኃይልና ጥበብ ለውጥን ያመጣል። አሁን የሚደረገው የሰላም ለውጥ፣ የተበላሸ ታሪክ የሚያስተካከልበትና የወደፊቱ ልዩ ስርዓት የሚመሰረትበት ወቅት ይሆናል በሚል ትልቅ ተስፋ ነው። የወያኔ አቋም አባይ ጸሀይና መስፍን ስዩም ከተለሙት የዕልቂት ፍጻሜ አቋም ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ የሚጠፋው ጠፍቶ ኢትዮጵያ ትኖራለች። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳንስ አሁን የቀረው አነስተኛ ርዝራዥ ኃይል ቀርቶ፣ ማናቸውን ኃይል ተቋቁሞ ድል ለመጎናጸፍ ያልተሞከረ ኃይል አለው። ለዚህም አንድ ጀነራል አይሻም። ከአሁን በፊት ኃይሉን ባይጠቀም ለወደፊት በኃላ ሁኔታ የሚያሰየው ይሆናል። ግን፣ ወያኔ እንደ ተፈጥሮውና አበቃቀሉ ድልብና ድርብርብ ጥፋት ለመፈጸም የተፈጠረ አመልና

ልክ አለው። ግን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያልቅበትን ትግስት ከፈጸመ ምርጫ የለውም፣ ጥንቃቄ እያረገ አስፈላጊውን ሰፊ እርምጃ እንደሚወስድ ገጽታውን አይቶ መፍረድ ይቻላል።

የወያኔ ኃይል እንደ ደርግ የሀገር ውስጣዊ ዕምቢተኛ-ኃይል የሚባል የዱር ሽፍታ አልነበረም። የነጻ አውጭ ግንባር ለየት ያለ ባህሪ አለው። ስለዚህ፣ በወራሪነቱ እንጂ በኢትዮጵያዊነቱ የሚታወቅ አይደለም። ወያኔ ጸረኢትዮጵያና የቅኝገዥ አገልጋይ (አስካሪ) ሆኖ እንዲታይ ያረገው ይኼው አጭር ታሪኩና የዕለት ድርጊቱ ነው። ወያኔ የነጻ አውጪ ኃይል በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዥ ለመባል ተቀባይነት ያላገኘ በመሆኑ ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ ቆይቷል። ወያኔ ያደረገው ሁሉ፣ ሞሶሊኒ ለራሱ ጥቅም ሲል እንዳደረገው ሁኖ ተቆጥሯል። ወያኔ ለመግዛት ካልቻልኩ ሁሉን አፈራርሼና ሕዝብ አበጣብጩ ወደ መጣሁበት እመለሳለሁ የሚለው ዕቅዱ በግንባሩ ላይ ይነበባል። ወያኔ ኢትዮጵያን ለሚቀጥለው መቶ አመት ከዚያም ይበልጥ ደቁሼ እገዛለሁ የሚለው ህልሙ፣ እንኳን የኢትዮጵያን ቀርቶ፣ ከዙፋን ያወጣውን የጌታውን ልብና ስልት አለማወቁን ያስረዳል። ግን ይህ ጥበበ የጀግናው ሕዝብ የኢትዮጵያኖች እንጂ፣ አስካሪ ያን ለማሰላሰል ብቃት የለውም። የከሀዲዎችና አስካሪዎች ልቦናና ጠባይ የሚገመተው በሌል ችሎታ ብቻ ነው፥ በጨካኝነት፣ በከሃዲነትና በድንቁርና ነው። ጌቶቻቸው ሕዝቡን ሲጨፈጭፉ የዕለት ድርጊታቸውን እያየ 'እኒህ ከሀዲዎች!' እንደሚሏቸው ፈጽሞ የሚያውቁት ጉዳይ አይደለም። ወያኔ ትርራይ የጀግና ጀጋ ያልነበራት ምድር አስመስለዋታል።

ወያኔዎች እንኳን ሀገር መንደር ለማያስተዳደር አንድም ችሎታ አልነበራቸውም። ግን፣ ድልድይ፣ ግንብ፣ ህንጻና መንደርን በፈንጅ ማፍረስ የተካኑበት ጥበብ ነው። በዚህ ሰልጥነው በቅኝ ገዥዎች ተመርተው ኢትዮጵያን ያህል ታላቅ ሀገር ለማስተዳደር በስልጣን እንዲቀመጡ ተደረገ። ኢትዮጵያ ያስተማረቻቸው ተገለው ኢትዮጵያኖች በማያውቁትና በሌሉበት በራሳቸው ላይ ገዥ ተቀመጠ። በሆቴል ቤት ስልጣኑና ዘውዱ ለአስካሪዎች ተላለፈ። ይህን አሰቃቂ ድርጊት የተባበሩት የዓለም መንግሥታት፣ የአፍሪካ አንድነት(አፍሪካን ዩንየን)፣ መንግሥታቶች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ኣምባሳደሮች፣ የዜና አሰራጮች፣ ሌሎቹም እያዩ እንዳላዩ፣ እያወቁ እንዳላወቁ መስለው፣ የአዲሱ የቅኝ ግዛት ስርዓት በኢትዮጵያ ላይ ሲፈጸም በዝምታ አዩ። የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን በግፍ የተነጠቀበትን ሁኔታ ብዙ ትውልዱ ሲያወሳው የሚኖር ነው። ይኸው የውጬ ኃይል፣ ታሪክህን የምታስታውስበት ታሪካዊ ቦታ ዳግም አይኖርህም በሚል ልቦናው፣ የሰራውና የሚሰራው መሆኑ ግልጽ ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሀገርና ሕዝብ ሆና እንዳትቀጥል ለወያኔ ሰርቶ የሰጠው መከፋፈያና መሰነጣጠቅያ ካርታ የአገር ማፍረሻ ስልቶች አንዱ ማስረጃ ነው። አስቀድሞ የሚጠፋውን ሕዝብ እግዜር ያውቃል። ኢትዮጵያን ለማፍረስ የተጠነሰሰው ሴራ ምናልባት ጠንሻሾቹን መልሶ የሚደመስስ ያልተተነበየ ድርጊት ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኸንን ሴራ ተገንዝቦ አንድነቱን ጠብቆና ጠላቱን ተከላክሎ ለመኖር ቆርጦ መነሳት አለበት። የአባቶች ብልህነትና የወጣቱ ቆራጥነት ኢትዮጵያን ይጠብቃል። የኢትዮጵያ ጠላት ሰፊ ጥበብና ኃይል ስላለው፣ ደካማው ሰው እንደ ወያኔ በወገኑና በሀገሩ እንዲያምጽ አድርጓል። ከሀዲ ሰው ከዚህ በኋላ ለሚደርስበት አለመፈጠሩን ይመኛል።

ኢትዮጵያ የዓለም ግልብጥብጦሽ መነሻ

የእስራኤሎችና የአረቦች ግጭት የጦር ሁሉ እናት መባል ይገባዋል። የአንደኛው ወይም የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ምክንያት አልነበረም። ግን፣ በዓለም ላይ ሰላም እንዳይሰፍን አድርገውታል። የሶስተኛው ዓለም ጦርነት መጠንሸሻ ምክንያት ይሆናል የሚል ስጋት አለ። አንዱ "እኔ እንድኖር አንተን ማጥፋት አለብኝ" ሲል፣ ሌላው "እንደ ሀገርና ሕዝብ አርጌ አልቆጥርህም፤ አጠፋሀለው" የሚባባሉ ህዝቦች ናቸው። ወያኔና ሻብያም እንዲሁ ናቸው። እንስማማ ብለው አንድ ቤት ቢገቡ፣ ኢትዮጵያ በምድርም በባህርም ያላንዳች ጦር ለዘላለም ትፈወሳለች። እነዚህን ህዝቦች የሚያምኑት ኃይማኖት ምን እንደሚያስተምራቸው አጠያያቂ ነው። የሁሉቱ ዘርፎች አማካይ ሕዝብ ከኢትዮጵያኖች የሚበልጥ የለም። ኢትዮጵያኖች ጥንት ከቦታው ለቀው ቢወጡም፣ የአሪት ባለቤትነቷን ፈጽማ ሳትለቅ፣ ቅርሷንና ኃይማኖቷን በክርስትና ዕምነቷ አጽድታ፣ እስልምናውንም ተቀብላ፣ ሁሉም ፋፍተው ለዘመናት እንዲኖሩ አድርጋለች። ማናቸውንም ሕዝብና ኃይማኖቱን አላጠፋችም፤ ሁለቱም ሲጎዷትና ሊያጠፏት ሲሞክሩ ቆይተዋል።

የዓለም ግልብጥብጦሽ ሲታቀድና ሲወጠን፣ ኢትዮጵያ የጽንሰ ሀሳቡ (የነ ኪሲንጀር፣ ኮኸን፣ ሄንዝ፣ ወዘተ ሴራ)መነሻ

ምድር ነበረች። አሁን በኢራክ፣ በሶርያ፣ በልቢያ፣ በየመን፣ እንዲሁም በቱኒዚያና በግብጽ የሚካሄደውና የተካሄደው የዓለም ግልብጥብጦሽ ላፈኑ ከኢትዮጵያ የተላለፈ ነው። ኢትዮጵያኖችን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር የመጀመሪያውን ዕንቅፋት ማስወገድ አስፈላጊ ነበር። ኢትዮጵያን መቆጣጠር፣ እንደውም ኃይሏን አሳንሶ በሞግዚትነት በእጅ አዙር መግዛቱ ትልቅ የፖለቲካ ኃይል እንደሚያገኙ በመረዳት ቀስ በቀስ እየፈተኑና ሙሉ ቅጥጥር ለማድረግ በቅተዋል።

ከብዙ ነገር እጃቸው የሌለበት ፕረዚዳንት ኦባማ የታላቅ መንግሥት መሪ ሆነው፣ የአንድ የንዑስን መንግሥት ምግባርና ባህሪ ሳይጠፋቸው ገለባብጠው፣ የወያኔ “የኢትዮጵያ አገዛዝ ዲሞክራታዊ” ነው በማለት ታሪካዊ ስህተት አደረጉ። ታላቁ የአሜሪካ መንግሥት የትንሽ ሀገር ባህሪን ለማሳየት ፈቃደኛ ሆነው፣ ወያኔን ከፍ አረጉ፣ አሚሪካን ዝቅ ብላ እንድትታይ አረጉ። ኦባማ እያወቁ የሰጡት ስህተተ አስተያየት ለወያኔ ታልቅ የሞራል ድጋፍ ሆነው። ወያኔ የዓለምን ጥልቅ ፖለቲካ ያልተገነዘበው፣ አንድን አካል ሲያጥላሉት እንጂ ሲያሞገሱት ዋስትናው ይጠፋል እሱም ይጠፋል። መለስ ዘናዊ ትንሹ ማስረጃ ነው። በአሜሪካ ጀነራል ፓወል ሰራተኞቸው በሰጣቸው አሳሳች ቃል ተመርተው በዓለም ሸንጎ ላይ የሚያስነውር የውሽት ምስክርነት ሰጥተዋል። ፕረዚደንት ኦባማም በተሰጣችው ተመሳሳይ የስህተት ቃል የኢትዮጵያ ሕዝብ ግፍ አገዛዝ እንዲቀጥል አድርገዋል።

አሜሪካ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ እጇቿን ያጠበችውና የተገለለችው ከኪስንጀር ዘመን ጀምሮ ነው። ኪሲንጀር በዘመናቸው ለኢትዮጵያ የተለሙት ያሁኗን ኢትዮጵያ ፌጥሯል ቢባል በታሪክ ትክክል ነው። ኪሲንጀር የኢትዮጵያን ንጉሥ ከሚጠሉት ክፍሎች ዋናው ነበሩ። ፕረዚዳንት ኒክሰን እንደ ፕረዚዳንት ኬኔዲ ኃይለሥላሴን ለማቅረብ ፍላጎት ነበራቸው። ንጉሡ አመሪካንን እንዲጎበኙ ለመጋበዝ ኒክሰን ፍላጎት ነበራቸው። ኪሲንጀር የሚያደርጉት እንቅፋት ሁሉ ኒክሰንን አልጥማቸው ብሎ ኪሲንጀር ለኒክሰን የሚያደርጉት የስልክ ጥሪ ወደ እሳቸው እንዳይተላለፍ ለጽሐፊያቸው ትእዛዝ ከመስጠት ደረጃ ደርሰው ነበር ተብሏል። ኪሲንጀር በደባ ይጠረጠሩ ስለነበር፣ ያችን ለመደባበቅ ሲሉ፣ ስለ ራሽያ አይሁዶች አሜሪካ ዕርዳታ እንድታደርግ ሲጠየቁ፣ እንኳን ከጀርመኑ አይሁዳዊ ቀርቶ ከማንም ሰው የማይጠበቅ አስተያየት፥“የሩስያ አይሁዶች በጋዝ ቻምበር ቢነዱ ኣሜሪካ ምን ይመለከታታል”በማለት ሰጡ ተብሏል። ይህ እጅግ አስቆጭ ሀሳብ፣ የሜሪካ አይሁዶችን ለሁለት ከፍሎ ቆይቷል። ግማሹ ከአይሁዶች ይገለል ሲሉ፣ ሌሎቹ ቅሉ ተጋኗል፣ ለይስሙላ እንጂ ብዙ ጠቅሟል ብለው ተከራከረውላቸዋል። ይህ ጉዳይ ሁሉም ሕዝብ ችግር እንዳልው ያመለክታል።

አሜሪካኖችና ኢትዮጵያኖች አንድ ትልቅ ተመሳሳይ ታሪክ አላቸው። ተወዳጁን ንጉሥ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሲን የገደለውን ይታወቃል። እንዲገደሉ ያዘዘው ግን አይታወቅም። እጅግ ተወዳጁን ፕረዚዳንት ኬኔዲን የገደለው ይታወቃል፤ እንዲገደሉ ያደረገው ኃይል ግን አይታወቀም። ኢትዮጵያኖች ንጉሣቸው እንዲገደል ያደረገው ሲታወቅ፣ ወይም አሚሪካኖች ፕረዚዳንታቸውን እንዲገደል ያረገው ኃይል ሲታወቅ እዚህም እዚያ መሪ ገዳዩ ይታወቃል። የፕረዚዳንት ኬኔዲን አሟሟት የምርምር መዝገብ ሕዝብ እንዳያየው ታሽጓል። ሕዝብ ካየው ወዳጅ ሀገሮች ጋር ግጭት ስለሚፈጠር፣ እንደገና ለ 25 ዓመቶች እንዲታሸግ ፕ/ትራምፕ እንዲያዙ ይጠየቃል የሚል ሀተታ በጋዜጣዎች ተነቧል። ከዚህ የበለጠ የአሜሪካንን ሕዝባዊ ህግ (ኮንስቲትውሽን) ገልብጦ የሚደፋ ስራ ወይም ሴራ ሊኖር አይችልም። በአሜሪኣክ ጠንካራ ህግ የሚያምነው ሰው ጥርጣሬ ማድረግ ይገባዋል። በዚህ ሀሳብ ሶስት እጅግ አሳሳቢ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ላንድ አፍታ እንደ ጥሩ ኢትዮጵያ-አሜሪካዊ ሆነን እንመልከተው፥

1ኛ የአሜሪካ ሕዝብ በታላቅ ክብር የመረጠውን ፕረዚዳንቱን ቀርቶ ዜጋውን በሴራ የገደለውን ትክክለኛ ፍርድ እንዲያገኝ ፍጹምና ትክክለኛ ልቦና ያለው ቆራጥ ሕዝብ ነው። ዕውነቱን ማወቅ ይገባዋል። ምስጢሩን አውቀው ሌላ 25 ዓመቶች ይደበቅ የሚሉት፣ እነሱስ? ስለ ፕረዚዳንታቸውና ስለአሜሪካ ሕዝብና ሕገመንግሥት የሚቆረቆሩ፣ እንደሕዝቡ ቆራጥ አሜሪካዊ አይደሉም? መቸም ሕዝብ ግልፍተኛ ስለሆነ ሁሉን ይወቅ፣ በጥበብ ይፈርዳል ማለትም አስቸጋሪ ግምት መሆኑም ይታወቃል።

2ኛ ከወዳጅ ወዳጅ (?)አገሮች ጋር ግጭት ይፈጥራል የሚል ፍራቻ አስተጋቡ። ማነው የአሜሪካንን ፕረዚዳንት ገሎ ወይም አስገድሎ እራሱን እንደ አሜሪካ ወዳጅ የሚቆጥር? ይኸ አባባል በዜና የተነገረ ነው። ፈጽሞ ከማይታሰብ ሀሳብ

ላይ ይጥላል። ሲገመት እንደተፈራውም ትልቅ ጠንቅ የሚያመጣ ይመስላል። ራሽያ፣ ኩባና ሌሎችም ጥቂት አገሮች ወዳጅ የሚባሉ አይደሉም። ግን ካሉበት፣ ምስጢሩ ይደበቅ ለሌላ መቶ ዓመት። ከዕልቂት ይሻላል። ልቦናን ገዝቶ ስሜትን መቀልበስ ተገቢ ነው።

3ኛ ሁሉም በሚስጢር ይኑር ግን፣ የተባለው ጠላት ወይም ወዳጅ ሀገር (ፐ/ ኬኔዲን ያስገደለ) በአሜሪካና በሕዝቧ ላይ ሌላ ጉዳት እንዳይፈጽም ቁጥጥር ተደርጎበታል ወይ ብሎ መጠየቅ መኃይምነት ይሆናል።

እንኳንስ ትናንሹ ሀገርና ሕዝብ ቀርቶ፣ ትላልቁ የሰለጠነውም ሀገር የአሜሪካ ኃይል የዓለም ሕዝብ ጥላና መከታ እንደሆነ ያውቃል። እንዲሆንም ይሻል። አሚሪካ የዓለም ሕዝብ የብልጽግና፣ የሰላም እና የተስፋ አድማስ ናት። በአሁኑ ወቅት፣ በኢትዮጵያ ገጠር ውስጥ ያለ ገበሬና ነጋዴ ከራሱ መንግሥት ይልቅ የአሜሪካ መንግሥት በሚያደርገው በጎ ነገር በይበልጥ ተማምኖ ተስፋ ያረጋል። ይኽ ዕውነተኛ አስተሳሰብ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ነው። በኬኔዲ መሞት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ተማሪው ዕንባ የረጨበት መሆኑን ይኽ ጸሐፊ የማይረሳው ያየው ታሪክ ነው። ኢትዮጵያኖች ሰለ ከኔዲ አሟሟት እንደ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪኮች አንብበው የማይጠግቡት እጅግ ሰማጭ ታሪክ አርገው ያዩታል።

*መንግሥቱ የጀመረው፣ መለስ የፈጸመው*

*መንግሥቱ ኃ/ማርያም ወይም በረከት ኃ/ስላሴ ይናዘዛሉ ብሎ ተስፋ ማድረግ፣ የሰውን ልክ ወይም የዓለምን ሁኔታ አለማወቅ ይሆናል። ከበረከት ይልቅ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ነሸጦት ዕውነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይናዘዛል ተብሎ ቢገመትና ቢናዘዝ፣ ቃሉ ከሰው ጆሮ ሳይገባ ተጠልፎ ይጠፋል። ያለንበት ሁኔታ ይህን ይመስላል። በፍጹም ቁጥጥር ስር ያሉ መሆናቸውን፣ ያላቸው መብት ከሂትለር እስረኞች እጅግ ያነሰ መሆኑን መረዳት ልብን ያረጋጋል። ግን ምንድን ነው ለማወቅ የምንሻው? አንዱና ዋናው፣ ንጉሡና አክሊሉ ኃ/ወልድ ከሌሎቹ 60 ባለሥልጣኖች እንዲገደሉ ያዘዘውን የውጭ ኃይል ለማወቅ ነው። ይህ ለኢትዮጵያኖች በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ይህን ማወቁ የሀገር ጥፋት ምንጩን ያሳያል። ሕዝብ ያለፈውን አውቆ የወደፊቱን ችግሩን በሚገባ እንዲጠነቀቅ ያረገዋል። ድጋሚ ሁከት እንዳይመጣ ከጠላት ወጥመድ የሚድንበትን መንገድ ያዘጋጃል። ስለዚህ የሆነውን ማወቁ አስፈላጊ ነው።*

*መንግሥቱ ኃ/ ማርያም ተራራውን ናደ። የመጀመርያውን የጠላት ዕቅድ ፈጸመ። መንግሥቱ ይኽን ካላወቀው ሊወነጀል አይገባም። መንግሥቱ ይህን በዕርግጥ የሚረዳው ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የተረዳው ግልጽ አመልካች ጉዳይ አለ። ይኼም እነ ኸርማን ኮሆን ባልተወቁ አለቆቻቸው ትዕዛዝ ያከናወኑት ሁለተኛው ታላቁ ሴራ ነው። የዚህ ሁለተኛ መፈንቅለ-መንግሥት እንቅስቃሴ ፈላጭ-ቆራጭ የሆነው ኃይል ምግባሩ ሰፊ ነበር። በሀገርና በውጭ ሀገር ያለውን የኢትዮጵያን ወገንና ተወላጅ ተቆርቋሪ ኃይል ሆኖ እንዳይነሳ፣ በዓለምእቀፍ ደረጃ ማፈኛ ስልት ማፈኛ ተዘጋጅቶለት ነበር። በዚህ አይነት፣ በውጭ ያለው ውስጥ ካለው ተባብሮ ለውጥ እንዳያመጣ በቀላሉ ድካሙን ከንቱ ለማድረግ ሴራው የጠበቀ ነበር። የሚደረገውን ሙከራ እያፈረሰና እያደከመ እነሆ እስከአሁን ድረስ ቆይቷል። ወያኔ ፈጽሞ ሊቋቋመው የማይችለውን ክብደት፣ በስውር በስሙ እየተከራከሩለት በወንጀል ተጠያቂ የሆኑት እነ ስዬና አድህኖም ከዓለም ድርጂት ቤት እንዲመስጉ አድርገዋል። የወያኔን አቅም አናንሰው። ወያኔ አለቆቻቸው ይኽን ማድረግ መቻላቸውን ሲያዩ "እዘዙን እንገድልላችኋለን!" የሚሉ ባንዳዎች ሆነዋል። በዚህ መሰረት፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች የወያኔን ጦር እያንከባከቡ ይዘው ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን በሚገባ ቢረዳም፣ የዓለም ሕዝብ ችግር እንዲህ መሆኑን ተረድቶ በትዕግሥት የሱን ቀን ይጠብቃል።*

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ እንዲቆርጥና ጸጥ ብሎ ለውጩም ለውስጡም እንዲገዛ መቅሰፍት መሳይ ፍዳ ቢረጭበትም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ታሪኩና የተፈጥሮ ባኽሪው ተስፋ ሳይቆርጥ በጽናት ይገኛል። በባዕድ ሀገሮች ያለው የኢትዮጵያ ወገን በሀገሩ ውስጥ ለሚደረገው ለውጥ ያለው አስተዋጽዖ ወደር የሌለው ነው። በጊዜው ትግል ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊትም፣ በቀሰመው ሰፊ ዕውቀት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመንግሥት አመሰራረትና ለሀገር ግንባታ እጅግ ተፈላጊ ምትክ የሌለው የሀገር ሀብት ነው። ለኢትዮጵያ ግንባታ ጣራ፣ ወለል፣ ግርግዳ፣ ማገር ነው። ይህ ዕርዳታ የጠራ እንዲሆን

ለማድረግ ወገን በያለበት መደራጀት አለበት። ይኼን የሚያካሂድ ዓለም አቀፍ የሆነ ጅርጅት በዋናነት መመስረት አለበት። የየአንዳዱ አስተዋጽዖ በምንም መለኪያ የሚመዘን አይሆንም። አንድ ዋና ድርጂት ለማቋቋም አዲስም ባይሆንም ያሉትን በመገንባትና በማቀነባበር ሊፈጸም ይችላል። ስለዚህ ተደራጅተው ያሉትን ሁሉ አጣምሮ አንድ ወጥ የሆነ አስተዋጽዖ ለሀገራቸውና ለወገናቸው እንዲያቀርቡ አስፈላጊው ዕርምጃ አሁንኑ መወጠን አለበት።

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር የገዥነት ሹመት ሽረት

ወያኔን በሥልጣን ላይ ያስቀመጠው ኃይል፣ መንግስቱ ኃይለማርያምን የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተፋው፣ ምትኩን በሰፊ ቅንብር ተዘጋጀ። መንግሥቱ ኃ/ማርያም የተመለመለበትን ስራ በሚገባ አገባደደ። በሁለተኛ ደረጃ የኢትዮጵያን መፈረካከስ ወይም የንጉሣዊ አገዛዝ አክትሞ ሌላ ዲሞክራሳዊ መንግሥት እንዳይቋቋም የዚህ የውጩ ኃይል ፍላጎት አልነበረም። እንደውም ለውጡ ወደዚያ አቅጣጫ እንዳያመራ ሰፊ ጥንቃቄ ተደርጎበታል። ስለዚህ፣ ችግሩ ወያኔን ከስልጣን ላይ ማውጣቱ ሳይሆን፣ የቀረው የኢትዮጵያ ኃይል እንዳያምጽና የወያኔን ዘውድ መጫን በመቃወም እንዳያራዝመው ነበር። መጀመርያ፣ መንግሥቱ ኃ/ማርያም በድብቅ ያለውዝግብ አገር ለቆ እንዲሄድ በረቀቀ ምስጥራዊ መንገድ ተዘጋጅቶ ነበር። የውጩን ኃይል ሚና ለመደበቅ፣ የመንግሥቱ ሾልኮ መውጣት የራሱ መላ ለማስመሰል ብዙ ተለባብሰው የቀረቡ ሁኔታዎች ነበሩ። የተደበቀውን ድብቅ ስራ መደበቂያ የተሰራጩ ማሳሳቻ ዜናዎችም ነበሩ። መንግሥቱ ኃ/ማርያም በድብቅ ካገር እንዲወጣ ተደረገ። የሚተካው መሪ ሰው ከግብረኃይሉ ጋር በቦታው እንዲሰፍር የተዘጋጀው ዕቅድ ምንም አይነት ውዥግብና ተቀዋሚ አካል እንዳይገጥመው እየተጠና መመሪያ ይሰጠው ነበር። ዋናው ሴራ የኢትዮጵያ ሕዝብና የቀሩት መሪዎች ወደ ለንዶን በተስፋ እንዲያተኩሩ ተደርጎ፣ የወያኔ ስልጣን መያዝ በአስቸኳይ ይፋጠን ነበር። በኢትዮጵያ ይኽ ሲፈጸም፣ በለንዶን የነበረውም የማታለያ ድርድር አብሮ ተፈጸመ። የኢትዮጵያ ሁለተኛው የመንግሥት ግልበጣ በዚህ ሁኔታ ተጠናቀቀ።

እጅግ የተቀነባበረ ነበር። መንግሥቱ ኃይለማርያም ብዙ ምስጢር ያዘለ ሰው ቢሆን፣ የውጩን ሁሉን ተንኮልና ሴራ የተገነዘበና የሚያውቅ ነበር ለማለት ያስቸግራል። የአፈጻጸሙ ሁኔታ ለሱም እንቆቅልሽ ሳይሆንበት አይቀርም። የተነገረውም ሌላ ሁኔታ ሳይሆን አይቀርም። አወጣጡን ሲያስምሩለት፣ እሱን ለመጠበቅ የሚያደርጉትና የወሰዱት ዕርምጃ መስሎ ታይቶት ይሆናል። የእነሱ (የኢትዮጵያ ስውር ጠላቶች)ሀሳብ ግን የያዘው ምስጢር በሌላ እጅ እንዳይገባ ከፍተኛ ጥበቃ ያደረጉለት ምክንያት ይኼ ነበር። ስለዚህ መንግሥቱ ኃ/ማርያም እሱን የሚረዱት እሱን የሚተኩትን ሽፍታዎች የሚያስለጥኑ መሆኑን ያውቅ ነበር ለማለት ያዳግታል። ቢያውቅስ ምን ሊያመጣ? ያወቀው እንደሌላው ኢትዮጵያዊ በተሌቪዥን ባየ ጊዜ ብቻ ነበር ማለት ይቻላል። ሀገር ለቆ ሌላ ሀገር እስኪገባ ድረስ፣ ጉዞውን ያስተካከለለት ይኼው የውጭ ኃይል ነው።

የመንግሥቱ ኃይለማርያም ተልዕኮ አጭርና የተመጠነ ነበር። እሱ ደግሞ ለውጥ አመጣለሁ ብሎ በልቡ ያሰበውንና የሚታየውን እንዲያደርግ ችላ ተብሏል። የመንግሥቱ ጥፋቶች ለመጪው ለወያኔው ኃይል እንዲበጁና እንዲጠቅሙ ቀደም ብለው የታሰበባቸው ነበሩ። መንግሥቱ ኃ/ማርያም የመሬትና የንብረት ውጥንቅጥ ሁኔታ ፈታሁ ብሎ ያደረገውን፣ ወያኔ ያለውጣ ውረድ ተጠቀመበት። መንግሥቱ ኃ/ማርያም የኢትዮጵያን ሕዝባዊ፣ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሰንሰለት እንዲበታተን አደረገ። ለወያኔ ትልቅ ስራ አቀለለት። የቀረውን ወያኔ በቤተክርስቲያንና በሞስክ እየገባ የአማራውንና የኦሮሞውን፣ የአፋሩን፣ የሶማሌውን፣ የከምባታውን፣ የሲዳማውን፣ የአኑኩንና የመላውን ኢትዮጵያዊ ጎሳ ኑሮ ቅጥ እያሳጣ ምስቅልቅሉን አወጣ። በነዚህ ንፁህ ሕዝቦች ላይ ጦርነት ጀመረ። የኢትዮጵያን ሕዝብ መልክና ታሪክ እንዲደመሰስና እንዲጠፋ አረገ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅርሶች እየተቦረቦሩ በኢሮፐያኖች እጅ እንዲገቡ አደረገ።

የሶስተኛው ለውጥ (በአንደኛውና በሁለተኛው አንጻር)

የውጩ ኃይል የአንደኛውና የሁለተኛው የሀገር ማናጊያ ለውጥ እንዳቀዱት ተፈጸመ። አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሶስተኛውን ለውጥ እየጠበቀ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠብቀው ለውጥ ግልጽና ዕውቅ ነው። ከዚህ ሁሉ ግፍ በኋላ ሰላምን ናፍቋል። ብልጽጋንም ይመኛል። እግዜር የምድር፣ የአየርና የሕዝብ ጸጋ የለገሰወ ሲሆን ለብልጽግና ወደር

የሌለው ነው። የጠፋውን ሊቀለብስ ጥበብና አርቆ የማስተዋል ጸጋ አለው። ግን የጥፋቱ ኃይል በቀየሰለት የመበታተን መንገድ ባለው ጥበብና ኃይል ይቀጥልበታል ወይ የሚለው ጥያቄ በየአንዳንዱ ሰው ጎልቶ ይታያል። በቅኝ አገዛዝ ስርዓት የተነሳሱ ሰዎች ሌላ ጥበብ አይታያቸውም። ማሸነፍን እንጂ መግባባትን ወይም መቻቻልንና መስማማትን እንደማያውቁበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል። ችግሩን የውጩም በሚገባ ያውቅለታል።

የውጩ ኃይል መሪዎቹን አጥብቆ መቆጣጠር መቻል አለበት። በየሰዓቱና ደቂቃው መንግሥቱ ኃ/ማርያም የሚሰጡት ምክርና ትዕዛዝ፣ እንዲበረግግ የሚያደርጉት ነበሩ ብሎ መገመት ይቻላል። በቀውጥ መንፈሱ የሚሰጡትን ትዕዛዝ በቅጽበት እንዲፈጽም አድርገውታል። በዚህ ዘዴ የነሱን ግብና አላማ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው እንዲፈጽም አርገዋል። ሀገር ገነባሁ ወይም አለማሁ እያለ ሲለፋደድ፣ እነሱ ደግሞ፣ በነሱ ጥልቅ ሴራ ሀገሩን እንዲያጠፋ ቀውስ ያዘጋጁለት ነበር። ትርምስ ሌባን እንደሚሸሽግ፣ በሀገሪቱ ትርምስ ሲሰራጭ የዋናው ዘራፊ እጅ እና ተንኮል እንዲደበቅና እንዳይታወቅ ተደርጓል። በዚያ ጊዜ፣ ማንም ወገን ያለዝናብ ጎርፍ መጣ ቢሉት የሚቀበልና የሚያምን ተላላ ሕዝብ ሆኖ ነበር። የዓለምን ስርዓቶችና ሕልውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰለጠኑት ሕዝቦች የበለጠ የሚያምንና የሚከተል በጎ ሕዝብ ስለሆነ፣ ከሂትለርና ከሞሶሊኒ በኋላ አንድ ሀገር በሌላ ሕዝብና ሀገር ላይ ያደርሳል ብሎ ያላመነውን ግፍ ፋሽሽት የተጠቀመውን የዘር ማጥፊያ መርዝ ተጠቅመውበታል። በክትባት አምክነውታል፣ ሸነኳኩለውታል። ዋናው ተቀዳሚው አላማቸው የኢትዮጵያን ጠባቂ መሪዎች፣ አገር ገንቢዎችና አስተዳዳሪዎች ማጥፋት ነበር። በሰጡት ትዕዛዝ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ተቀብሎ በፈጸመው ኢትዮጵያን ባዶ አድርጓታል። በዚህ መሰረት የውጩ ኃይል በቂም በቀል ተነስቶ መንግሥትን በእጅ አዙር አጥፍቷል፣ ሕዝብን አውድሟል።

መለስ ዘናዊ፣ መንግሥቱ ያልፈጸመውን የኢትዮጵያ ጠላት ያቀደውን አላማ ከፍጻሜው ኣንዲያደርስ የተመለመለ አስካሪ ነበር። በኢትዮጵያ ላይ በወያኔ የደረሱት ጥፋቶች፣ ለዓለም መቅረብና መታወቅ ያለባቸው አሰቃቂ ድርጊቶች ናቸው። ቀርበዋል። ሕዝብ በመርዝ ተበክሎ አልቋል። ሕዝብ ተወሮ፣ ቤቱ ተቃጥሎ፣ ንብረቱን ተቀምቶ ሀገሩን ጥሎ እንዲሸሽ ተደርጓል። በስደት ኢሮፕን አጥለቅልቋል። አንዱ  ወገን ሌላውን እንዲያጠቃ እየተገፋ መሳሪያ እየታደለ ኢትዮጵያኖች በሀገራቸው ተባብረውና ተስማምተው እንዳይኖሩ ተደርጓል። በተለያዩ ግፍ ስራዎች ቁጥሩ ከሚሊዮን የማያንስ ግለሰቦች እየተለቀሙ እንዲጠፉ፣ በእስር እንዲማቅቁ፣ በጭካኔ አገዳደል ሕይዎታቸው እንዲጠፋ ተደርገዋል። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ኤትዮጵያኖች በሚኖሩበት ሀገር ሁል፣ እንደውጭ ዜጋ ተስማምተው እንዳይኖሩና እንዲበታተኑ በማድረግ የውጩ ኃይል በዚህ ሴራ ተባባሪ በመሆን የተለያዩ የስውር የግፍ ስራ በኢትዮጵያኖች ላይ ፈጽመዋል። ኢትዮጵያኖች ያለምንም ፍራቻ ይህን ግፍ ለመቋቋምና ለማቆም በየአሉበት መደጋገፍ አለባቸው።

ሶስተኛው የሕዝብ የዲሞክራሳዊ ለውጥ

ለሶስተኛ ጊዜ የሚሆነው የመንግሥት ለውጥ በመልኩም፣ በድርጊቱም፣ በፍጻሜውም የኢትዮጵያኖች ይሆናል የሚል እምነት አለ። የዚህን ውጤት የሚያሳየው የሕዝቡ ንቃትና ትብብር ነው። ወያኔ በውጩ ኃይል እየተመራ፣ ሕዝቡ እንዲከፋፈልና እንዲበጣበጥ ሲያደርግ መቆየቱ፣ አሁን ሕዝብ እንዲነቃና ሴራውን እንዲያውቅ አድርጎታል። ስለዚህ፣ ማንም ኃይል ሕዝቡን ከመብቱና ዲሞክራሳዊ አስተዳደር ፍላጎቱ የሚያቆመው ምንም ኃይል አይኖርም። እንደተለመደው፣ የዘመኑ ቅኝ ገዥዎች ጥንታዊ ስርዓታቸውን በመጠቀም ወደኋላ ላይሉ ይችላሉ። ስለዚህ፣ ሀገርን ሲወሩና ሲገዙ፣ አንዱ ሰው ሌላ ወገኑን እንዲክድ በማድረግ ተስማሚ ከሀዲ አገልጋይ አስካሪ እየመለመሉ ነው። ዘዴው እየረቀቀ ስለሄደ ሕዝብን ለመቆጣጠር አያሌ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ጥበቦችን ይጠቀማሉ። ሰው የሚታለልበትንና ቤተሰቡን፣ ጓደኛውን፣ ወገኑን እንዲክድ የሚያደርገውን የንዋይን ኃይል እየተጠቀሙ ነው። ስለሆነም፣ የገንዘብና የስልጣን ጥማት ያለው ሰው ባህሪውና ሕሊናው ፈጽሞ እንዲቀየር ያደርጉታል። በዚህ የክህደት ባህሪ የተበከለው በርካታ ነው። ኦሮሞውን በኦሮሞ ላይ፣ አማራው በአማራ ላይ፣ ወዘተ እያሰማሩ የሕዝብን ትብብርና አንድነት ሊያጠፉት ችለዋል። ከጊዜ በኋላ ሕዝብ ይማራል ይነቃል። ስለሆነም፣ መሰናክል እየሆኑ ያስቸገሩት የሕዝብ ንቃትና ኃይል ከከሀዲነት ወደ ውስጥ አርበኛነት ሚና ሊለውጣቸው ይችላል። ከዚያም በላይ፣ የወያኔ አገልጋይ የነበሩት አያሌ የውስጥ አዋቂ እየከዱ

የወያኔን ሰፊ የጥፋት ስራ ማጋለጥ ጀምረዋል። ይህ የሕዝብን ንቃትና ጥንካሬ ያመለክታል። ቀጥሎም ወታደሩና ባለሥልጣኑ እየከዳ ወደ ሕዝብ እንደሚሄድና ወያኔ ርቃኑን እንደሚቀር አያጠራጥርም። ስለዚህ፣ የሶስተኛው መንግሥት ለውጥ በዕርግጥ የኢትዮጵያ የዲሞክራሳዊ መንግሥት መመስረቻ የሚሆን ነው።

የለውጥ ፋናዎች – የኢትዮጵያ ህልውናዎች

ከዚህ በኋላ፣ ኢትዮጵያ በማንም ዜጋዋ እንባና ደም አታድግም፣ አትበለጽግም፣ ሰላምንም አታመጣም። ማንም ሰው፣ ወገኑን የጎዳና የበደለ፣ ሀገሩን የከዳና አሳልፎ የሰጠ፣ በላቡና በጉልበቱ ለጎዳው አስፈላጊውን ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል። ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ካልሆነ በስተቀር፣ የማንም ሰው ዕውቀትና ጉልበት በከንቱ ሳይባክን ለሕዝብና ሀገር ጥቅም እንዲውል፣ አዲሲቱ ኢትዮጵያ ጠይቃ መቀበል ይኖርባታል። ይህ ህልውና፣ ያለፈው ግፍ ዘመን ማብቂይና የአዲሱ ዘመን መከፈቻ ይሆናል።

ዲሞክራሲ እጅግ አስቸጋሪ ፍልስፍና ነው። ለማክበርም ለማስከበርም አዳጋች ነው። ትርጉሙና ልማዱ በቀላሉ በስራ ለማዋል ላለመደው ሕዝብ ይከብዳል። ለማወቅ፣ ለመማርና ፍልስፍናውን ለመገንዘብ ሰፊ የግል ምርምርን ይጠይቃል። ዲሞክራሲ የግለሰብ እንጂ የግሩፕ ሕግ የለውም። መብት የተናጠል እንጂ የግሩፕ ሕግ የለም። ለምሳሌ አይነስውር መብት ይሰጠዋል። አይነስውሮች ሁሉ በዚያ ተናጠል መብት ሊጠቀሙ ይችላሉ። በዚሁ አንጻር ደንቆሮዎች፣ አካለ ስንኩሎች በተናጠል በተደነገገው መብት ሊጠቀሙ ይችላሉ። ይኸ ማለት፣ አይነስውሮች፣ ደንቆሮዎችና አካለ ስንኩሎች በጅምላ የተሰጣቸው መብት የለም። ሊኖርም አይችል። አንድ ሰው የሶስቱም መብት ቢኖረው በተናጠል እንጂ በጅምላ ለሶስቱ የተደነገገ ህግ ስለሌለ፣ መብቱ በያንዳዱ ህግ መሰረት ላይ የሰፈረ ይሆናል። ሌላው ምሳሌ፣ በወሎ ሕዝብ የመብት ጥያቄ ላይ የተመረኮዘ ይሆናል። ወሎ አያሌ ዘርፎች፣ ባህሎችና ቋንቋዎች የሚኖሩበት የግዛት ምድር ነው። የነዚህን ሕዝብ መብት የሚጠብቅ አንድ አጠቃላይ መብት የለውም፣ አይኖረውም። ከላይ የተጠቀሱት የተናጠል የግለሰብ መብቶች ደግመው ሊጠቀሱ ይቻላል። ስለዚህ፣ የትግራይ ሕዝብ ከወሎ ወይም ከወለጋ ሕዝብ የተለየ መብት የለውም። ግን፣ የትግራይ ሰውና የወሎ ሰው በሀገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ህግ መሰረት የየአንዳዱን ሰው መብት ግዛቶቹ ያስከብራሉ። አፋር ከኢትዮጵያ ጸጋና ቅርስ እንዳይካፈል ተገፍቶ ባህር እንዳይጣል መብቱ (የየአንዳንዱ ሰው መብት) ይጠብቀዋል። ማንም አስገድዶ ከሰፊው ግዛት ተሸርፎ እንዲወጣ ሊያደርገው አይችልም። የአፋሩ ሕዝብ መብት አለው። እንዲሁ ትቂት ወይም ብዙ ያፋር ሰውች ምድር ቆርሰው ቢገለሉ፣ የሌላው ሕዝብ መብት ያግዳቸዋል። ይኸ የዓለም ስርዓት ነው። ኃይልና ጦርነት ሊንደው ይችላል። ኃይልና ጦርነት ስርዓቱንና ሕጉን ሲቀይሩት ታይተዋል።

አንድ ሀገር ሁሉን የዜጋዋን ዕኩል መብት መጠበቅ ግዴታዋ ነው። የሀገሪቱን ጸጋ ለወገኖቿ ጥቅም ታውላለች፣ ጸጋውንም ትጠብቃለች። በአንድ ሀገር ክልል አድማስ ውስጥ ያለ አየር፣ ምድር (አፈር)፣ ውሃ የሀገር ሕዝብ ጸጋ ነው። አንድ ሀገር ኃይል ሲያንሳት የማይቆረሰውን ምድር ታስቆርሳለች፤ የማይከፈለውን ወገኗን በማስወረር ታጣለች። ኃይል ሲኖራት የዜጎቿን መብት ታስከብራለች። ድንበሯን ትጠብቃለች። የሀይል ነገር ውጣ ውረድ ነው። ኢሳኢያስ ታግሎ በኃይል ኤርትራን አስገንጥሏል። የዓለም ሕዝብ ሁሉን ማስተካከል ተስኖታል። እንደመለስ ያለ ሰው በስልጣን መቀመጡ ባያስደንቅም፣ ዓለም ደረጃ መድረሱ የዓለምን ስርዓት እጅግ አሳንሷል። አፍሪካ ብዙ መጥፎ ሰው ፈልቆባታል። መለስ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካና የዓለም ቅርሻ ጠለት ነው። ተከታዮቹ በአፈቃላጢነቱ እጅግ የተማረኩ አሉ። አለመብሰል ነው። በከህደቱ ስራ ትክክሉ ነገር አልታይ እያላቸው ሲመጻደቁ ይታያል። የመብሰል ጉዳይ ነው። የብዙ ዕጦት ጉዳይ ነው። በግዛቷ፣ ወደቧ፣ ድንበሮቻ፣ በወገኖቿ የተፈጸመው የፍርድ ቀን ያገኛል።

የለውጥ ዕቅድ

የለውጥ መግቢያ ሶስት አማራጭ መንገዶች አሉት። አንደኛው፣ ወያኔ ሲፈርስ ጥሎ ወደመጣበት መጓዝ ነው። ፈጽሞ የማይሳካ ዕቅድ ነው። ከየሀገሩ የሰበሰባቸው ኢጋዚያን የሚያግዱት ይሆናል። የሚቀበላቸው ሕዝብ አይኖርም። ዕልቂት በትግራይ ይፈጸማል። መሪዎች በየዛፉ ተሰቅለው የሚታዩ ይሆናል። በኤርትራ ሲጨፈር በኢትዮጵያ ሀዘን ይሆናል። ይህን ለማቆም ኢትዮጵያ ገና የተደላደለች አትሆንም። ባዶ የቀረውን ማስተካከልና ሀገርን የመጠበቅና

የመገንባት ጫና ውስጥ ቶሎ ትገባለች። ይኽ ምርጫ ታስቦ ድሮ የቀረ ስለሆነ፣ እነ አባይ ጸሐይና በረከት ስሞን ይህ እንደማይሆን ተገንዝበው ወደ አሜሪካ መጥተዋል። መስፍን ስዩምና ብርሀነ ገ/ክርስቶስ ሌሎቹም አይመለሱም። ሁለተኛው ምርጫ ወያኔዎች እየታገሉ ይቆያሉ የሚለው ነው። እንዳሉ አብዮት ይፈነዳና ወያኔዎች እጅ ከፍንጅ በያሉበት ይያዛሉ። ይክ ጸሐፊ ከዚያ በኋላ የሚመጣውን ውጥንቅጥ ለመግለጽ ያቅተዋል። ፍጻሜው ግን ድል ለኢትዮጵያኖች ሆኖ ሀገር ተረጋግቶ ሀገሪቱ መደራጀት ትጀምራለች። ኢትዮጵያ ቆሳስላና ደምታ ትቀጥላለች። ሶስተኛው አማራጭ ይህ ጸሐፊ እጅግ የሚተማመንበት ኢትዮጵያኖችን እጅግ የሚያኮር ታሪክ ይሆናል የሚለው ነው። የኢትዮጵያኖች ለውጥ በሽግግር መንግሥት አማከይነት ይፈጸማል። የዚህ አካሄድ ዕቅድ ንድፍ ሀሳብ ተዘጋጅቷል። እጅግ ባጭሩ በትቂት ዓረፍተ ነገሮች ይገለጻል።

የሽግግር መንግሥት

የሽግግር አማካሪ መንግሥት፣ የሀገሪቱ ሕዝብ በአውራጃ፣ ወረዳና ቀበሌ የተደራጀው እየመረጠ በሚልካቸው አማካሪዎች፣ የፖለቲካ ተቃዋሚ ሆነው በቆዩት በውጭና በሀገር ውስጥ የፓርቲና ድርጅቶች ተወካዮች፣ ከተለያዩ የሀይማኖት ክፍሎች በሚላኩ ልዑካን፣ በምሑራንና በአስተዳደርና የህግና ሌላ ዘርፍ ሊቆች፣ በተለያየ ዕውቀትና ምግባር የታወቁ ግለሰቦችንንስ አባት እናቶችን ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፋ ያለ አካል የሀገሪቱ ባለሥልጣን ሆኖ ይቋቋማል። ስራው ቆሚ መንግሥትን ለመመስረትና ሕገመንግሥትን አዘጋጅቶ ለማቅረብ ብቻ ይሆናል። ይህ በሰፊ ጥናት፣ ምርምርና ምክር የሚካሄድ ስለሚሆን፣ ባንድ ጊዜ የሚቋጠር አይሆንም። ጊዜአዊ አገዛዝን መጀመሪያ መስርቶ፣ ቋሚውን መንግሥትና ሐገመንግሥት በሁለተኛ ደረዳ የሚያካሂድበትም ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። የሚፈጠረው የሽግግር አማካሪ መንግሥት በሰፊ ምክክርና ጥናት የሚወስደው ዕርምጃ ሊሆን ይችላል።

ቋሚ መንግሥት እስኪፈጠር ድረስ ያለው መንግሥት በግዜያዊው የሽግግር አማካሪ መንግሥት እየተመራ፣ ምግባሩን ባለበት ይቀጥላል። የሽግግር አማካሪ መንግሥት የሀገሪቱን መሪ በምርጫ ያቆያል ወይም መርጦ ይተካል። በጥናትና በምክክር የሚወስነው ይሆናል። የራሱን ፕረዚዳንት ወይም ዋና ጸሀፊ ይመርጣል። አያሌ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል። በነዚህ ኮሚቴዎች እየተጠና የሚቀርበው በውይይት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው ለውሳኔ ይቀርባል። የሽግግሩ አማካሪ መንግሥት የበላይ ስልጣንነቱን ይዞ ማናቸውም የጸጥታ ጥበቃ ኃይል በቁጥጥሩ ይሆናሉ። ማናቸውም የዚህ ክፍል በሌላም ዘርፍ ያለው የመንግሥት አሰራር ባለስልጣን ያለ ግዜያዊው የሽግግር አማካሪ መንግሥት ወሳኝነትና ደንጋጊነት ውጭ ስልጣን አይኖረውም። በሚገኘው አስተዳደር መልክ እየሰራ ይቆያል። ችግር ሲፈጠር በግዜዊው የሽግግር አማካሪ መንግሥት አማካይነት የሚሰጠውን መመሪያ ተከትሎ ርምጃ ይወስዳል። አስፈለጊ ካልሆነ በቀር፣ የግዜያዊው የሽግግር አማካሪ መንግሥት ጣልቃ በመግባት በአስተዳደሩ ስራ ላይ እንቅፋት አይሆንም። ያለውም መንግሥት አስተዳደር የፖሊሲ ለውጥ ያለ ሽግግሩ አማካሪ ፈቃድ አያደርግም። ቋሚው መንግሥት ተመስርቶ የረቀቀው ህገመንግሥት ጸድቆ በስራ እስኪውል ድረስ ማናቸውም ኢትዮጵያ የሰራው ወንጀል ካለ ጽጥታ አናግቶ በቁጥጥር እንዲውል ካልተደረገ በስተቀር፣ የሚጠየቅ አይሆንም። ምንም ዓይነት ርምጃ እይወሰድበትም። ይህን ጥሶ በሌላ ሰው ላይ ርምጃ የወሰደ በቁጥጥር ስር እንዲገባ ይደረጋል። የማንም ሰው በደልና ወንጀል የሚፈተሽና ፍርድ የሚሰጠው በአዲሱ ሕገመንግሥት አማካይነት ይሆናል። የሽግግሩ አማካሪ መንግሥት መቋቋምያና የስራው ማካሄጃ መመሪያ የሚሆን ሰፋ ያለ የዕቅድ ንድፍ ተዘጋጅቶ ይገኛል። ከዚያም በላቀ ተሟልቶ በስራ የሚውል ይሆናል። ያለውና የሚፈጠረው ሁኔታ የሽግግሩ አማካሪ መንግሥት በኢትዮጵያ ተቋቁሞ ስራውን ያለዕንቅፋት እንዲጀምርና እንዲያካሂድ፣ የዓለም መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት በተለይ የአሚሪካና ሌሎች መንግሥታት እንዲደግፉትና ለዚሁ የሚጠቅም አስፈላጊ ዕርዳታ እንዲያበረክቱ ይጠየቃሉ። ከዚህ ደረጃ የሚያደርሰው አንድ አካል መፈጠር አለበት። ይህ በእርግጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊወጠን የማይችል ይሆናል። ስለዚህ፣ በውጭ ያሉ የኢትዮጵያ ወገኖች ባስቸኳይ በአንድ ሀገር ምናልባት በዋሽንግተን ዲ ሲ አካባቢ አያሌ ወገኖች በሚገኙበት ቢቋቋም ታላቅ እርምጃ ይሆናል።

መደምደሚያ

በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ካለበት ወደ ሌላ ችግር በማናቸው ሰዓት ተለውጦ መፍትሔው በቀላሉ በማይገኝ አስጊ ሁኔታ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ይህን ለወያኔ ማስረዳትና እንዲያውቀው ማድረግ ፈጽሞ የማይቻል ይመስላል። በሌላ የውጭ ኃይል ተወጥሮ የተያዘ ስለሆነ የራሱ ህልውና ስለሌው፣ ያንንም መገንዘብ ይጠቅማል። ምናልባት በህመም እያመካኙ ሸሽተው ከሀገር የወጡት ከሚና ውጭ ስለሆኑ፣ መቀሌ ሁነው ሀገሪቱን ሊገዙ ከተነሱት የባሱ ወይም የተሻሉ ይሁኑ አይታወቅም። በዕውነቱ እንደዚህ ማሰቡም ተነቃፊ ሊሆን ይችላል። አንዱን ሰይጣን ከሌላው ማመዛዘን 'አልወልድ ያለ ዕርጉዝ አገባ' ማለት ይሆናል። ነገሩ ግን፣ በዚህ ቁርጥ ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ ሌላ አካል አይጠበቅም። 'ቅጠል የከበደው ግንዱን አለ'ይሆናል። በትግራይ ያሉት ከሌላው ይበልጥ እጅግ የመከኑ ስለሆኑ፣ አንዲት ፍንጭት ነገር እስኪያሳዩ በነሱ ላይ ምንም አይነት ተስፋ ማድረግ ዝቅተኛ መሆንን ያንጸባርቃል። ዋናው ቁምነገርና ትልቁ ምግባር ትግራይ ራሷ ከነሱ ቁጥጥር ውጭ እንድትሆን ማድረግ ነው። ለኢትዮጵያና ወገኗ የተሰለፉትን ቦታ መስጠትና ማበረታት ይገባል። በነሱ አማካይነት ትግራይ ተቀዳሚ ቦታዋን ትይዛለች።

ኢትዮጵያኖች በበለጠ ቶሎ መደራጀትና መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው ከላይ የተዘረዘርው ያሳስባል። የወያኔ ኃይል በጭካኔ የተንቀሳቀሰውን ሕዝብ እያፈነ ስለሆነ፣ ከውስጥ ያለው በዚህ ሁኔታ ለመደራጀት ስለማይችል፣ ቀን እስኪመጣ ድረስ ከውጭ ያለው ወገን ይህን በመገንዘብ ቅድመ ምግባሩን መወጠንና ማካሄድ ይገባዋል። ይህ ድርጊት ከተጠቀሰው ቦታ በኢትዮጵያዊያኖች ሊወጠን ይችላል። ስራው እንዲቀጥልና እንዲከናወን ከወያኔና ሻብያ ጋር የተነካካውንና ሰርጎ ገብ እየመነጠረ ከድርጅቱ እንዲገለል ማድረግ ይኖርበታል። ሆኖም ኢትዮጵያ ስለሆነች ሁሉን ማከተት ተፈላጊ ይሆናል። በጥንቃቄ እየተጠኑ መቀላቀል የሚገባቸውን ሰዎች ማከል ተገቢና አስፈላጊ ነው። በዚህ ተመሳሳይ ምግባር ቀደም ብለው የተዘጋጁትን ሁሉ መሰብሰብና አገርወጥ ድርጅት እንዲወጣላቸው ማድረግ የሚቀና ስለሆነ ይህ አማራጭ ታስቦበት በስራ እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚያም በነሱ አነሳሽነት ሌላውን ለማስተባበር ቶሎ ዕቅድ አውጥቶ መሰማራቱ ወቅቱ አሁን ነው።

የትግራይ ሰዎች በተለይ በውጭ ሀገሮች የሚገኙ ለወያኔው መንግሥት በራሳቸው ስም መልዕክት ማስተላለፍና ወያኔ የቀረበለትን ምርጫ እንዲቀበል መወትወት አለባቸው። ወያኔ ከውጭ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይስ በራሱ ሰዎች የሚነገረውን የቱን አክብሮ እንደሚቀበል አይታወቅም። ዕርዳታ የሚያግተለትለትን አዛዥ ጌታውን ትቶ/ንቆ ሌላውን ይሰማል ማለት ዘበት ነው። በስልጣን የመቆያህ ዘዴ ይህን ሰው/ጎሳ (ጠላቶችህን)መግደል ነው እየተባለ እንደ ዕውር ሲመራ የቆየን አስካሪ በምክር እንዲለውጥ መሞከር ስለ ቅኝ ገዥዎች ዘዴዎች አለማወቅ ይሆናል። ሊሆን የሚችለው አጋዛያኑ እየተበተነና እየተበታተነ እንዲሄድ በማድረግ ወያኔ ዕርቃኑን እንዲቀር ሲሆን ብቻ ነው። ያን ጊዜ ወያኔ መካሪም አጋዥም ስለማይኖረው የአሞራ እራት መሆኑን አውቆ ይሞታል። ይኼንን ፍጻሜ እንዲገባው በግልጽ ለማስረዳት ተስፋ የማይቆርጡ እንድዚህ ጸሐፊ ያሉ ይኖሩ ይሆናል። ከሆነ፣ በተናጠል ሳይሆን የትግራይ ሰው ተማሪውንና ምሑራኑን ጨምሮ (ካሉ)በጅምላ ወያኔ እንዲስማማ ጥያቄ ቢያቀርቡ ክብደትና ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል። ተስፋ አለመቁረጥ ተገቢ ነው። ስለዚህ፣ ይህንን አካሄድ በጣም ማበረታታት ያስፈልጋል። ይህ ድርጊት ሌላ ብዙ ጥቅም አለው። የትግራይ ሕዝብ ከወገኑ ጋር እንዲቆም ያነቃቃል። ከዚያም በላይ፣ በዚህ መጨረሻ ቀን የወያኔን ግፍ ስራ ተቃውሞ ከኢትዮጵያኖች ጎን መቆም ታሪካዊ ስራ ነው። በወገናቸው ላይ የሚደርሰውን ግፍ መቃወማቸውን በግልጽ ያሳያል። ወያኔ የራሱን ሞት ጽዋ ለትግራይ ሕዝብ ማላከክ እንዳይችልና የትግራይ ሕዝብ ያለኃጢያቱ እንዳይወገዝ መከላከል ያስፈልጋል። እስከዛሬ በስማቸው የነገደው በቂ ነው። ቅዋሜአቸውን ወጥተው ማሳየት አለባቸው። ለመናገር ነጻነታቸው ታፍኖ የቆየ ነው ቢባል አሁን እንደሌላው ኢትዮጵያዊ እኩል የሆነ የመስዋዕትነት ዕድል አላቸው። የተላቀሱበት መለስ ዘናዊ እነሱን፣ ወገን ሀገራቸውን ለከፋ ጥፋት አድርሷል። ሰየ፣ አባይ፣ በረከት፣ ብርሀነገብረክርስቶስ፣ ወዘተ ለዕልቂት አጋልጠው የመሸሻ ፎርማታ እየያዙ ናቸው። ወያኒ በኖ ይጠፋል፣ ኢትዮጵያ ትቀጥላለች። ይህን የተረዳና የሚረዳ መሰረቱን ያለቀቀ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈራጅ ይሆናል።

የውጩ የኢትዮጵያ ጠላት ከዚህ በኋላ የሚመኘውንና የሚፈልገውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲረዳው አይሻም። ከዚህ

በኋላ፣ ራሱ ታንኩን ይዞ ይግባና ከቻለ ሀገርን ወሮ አዲስ አበባ ገብቶ ይግዛ። ከዚህ በኋላ፣ ኢትዮጵያ በአስካሪዎች አማካኝነት በሞግዚትነት አትገዛም። ከቴላቪቭ፣ ለንደን ወይም ኒውዮርክ ሆኖ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር የማይቻልበት ጊዜ ገብቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ውሳኔ ማንም የማይሽረውና የማይገለብጠውን ኃይል ለማሳየት ራሱ፣ ልጁ፣ የልጅ-ልጁ ታጥቆና ቆርጦ ተነስቷል። ዋናው ኃይሉ አንድነቱ ነው። የጠላት ስውር ኃይል ደግሞ፣ አንዱ በሌላው ላይ እንዲያምጽ እያደረገ ነበር/ነው። ያልተማረውን፣ ተላላውንና ከሀዲውን ሰው በዘዴ እየደለለና እየገፋፉ በእጁ ግፍ ስራ እንዲፈጸም አርጓል። ይህን ጥበቡንና ዘዴውን ሰው በዐዕምሮው እየበለጸገ ሲሄድ የጠላቱን ዘዴ ሲረዳ ከወጥመዱ ራሱን ነጻ ያረጋል። አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የጠላቱን ጥበብ ተረድቶ ራሱን ነጻ አወጥቷል። ዳግማዊ ወይም ሳልሳዊ የሚባለውን የጀግንነቱን ስራ ለመፈጸም ተነስቷል።

“ደምህ ደሜ ነው!”

ስለ ጸሕፊው

•ዘውገ ፋንታ በወሎ ክፍለሀገር በደሴ ከተማ ተወልዶ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርቱን በወ/ሲጊን ኮምፕሪሄንሲቭ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመጀመሪያ ምሩቆቹ አንዱ በመሆን ተመርቋል።

•በቀ/ኃ/ሥ/ዩኒቨርሲቲ እየተማረ በካርታ ድርጅት ተቀጥሮ በመስራት እያለ፣ ከተባበሩት መንግሥታት ስኮላርሺፕ ለካርታ ስራ ጥናት ተወዳድሮ ከተሳተፉት ሁሉ ሁለተኛ በመሆን ስላለፈ፣ ጥናቱን በእንግሊዝ አገር እንዲከታተል ተላከ።

•ጥናቱን በጂአደሲ፣ ፎቶግራሜትሪና ካርቶግራፊ አጠናቆ በታላቅ ክብር ተመርቆ፣ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ የበላይ ካርቶግራፈር ተብሎ በካርታ ድርጅት አገልግሎቱን ቀጠለ። የካርታ አሰራር በዕቅድ እንዲሰሩ ዕቅዱን አወጣ። ከፍተኛ አገራዊ ፕሮጀክቶች እየተመደበ ሰራ። ለብዙ የመንግሥት ቅርንጫፎች፣ ጦር ሚኒስተር፣ አገር ግዛት፣ ባንክ፣ ሲቭል አቪኤሺን፣ ቱሪስት ድርጂት በሌሎችም ክፍሎች እየተመደ አገልግሏል። ከኢትዮጵያ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪአ መንግሥታት ‘አችቭሜንት ሰርቲፊኬት’ የምስክር ወረቀቶችንተቀብሏል።

•ለትምህር አሜሪካ በመምጣት ከኦሪገን ስቴት፣ ፖርትላንድ ስቴትና አርጎሲ ዩኒቨርሲቲ ባችለርና ሁለት ማስተር ዲግሪዎችን ተቀብሏል።

•በቺካጎ ስኩል ኦፍ ፕሮፌሽናል ሳይኮሎጂ የኦርጋናይዜሽናል ሊደርሽፕ የፒ ኢች ዲ ፕሮግራም የ 3 ኛ ዓመት ተማሪ ነው።

•በአሜሪካ፣ ለብዙ የግልና የመንግሥት መ/ቤቶች በተለያዩ ሙያዎች ሰርቷል። ከነሱም ፖርት ኦፍ ስያትል፣ በሳውንድ ትራንዚት፣ በስያትል ከተማ ማ/ቤት፣ በታኮማ ት/ቤቶች በኢንጂነሪንግ ድፓርትሚነት፣ በፖርትላንድ ከተማ ማ/ቤት፣ በፋውንዴሽን ሳይንስ ከምፓኒ እና በሌሎች ድርጅቶች ሰርቷል። ብዙ ታላላቅ ፕሮጀክቶችን አጠማቋል።

ሁሉም ባይሆን ትቂቶቹ ከላይ በየገጹ የሰፈሩት አዲስ ጥናትፕችና ህሳቦች ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ ማንም ሰው ከፊሉን ወይም ሁሉንም በቃል ወይም በጽሑፍ መልክ ቆንጭሎ በመጥቀስ ከተጠቀመበት፣ የጸሐፊው ስም እንደምንጭ ሆኖ እንዲገለጽ በትህትና ይጠይቃል። በሚነሳ ጥያቄ ላይ ተጨማሪ ገለጻም ለመስጠት ምንጊዜም ፈቃደኛ ነው። በሚከተለው ኢሜይል ጸሐፊውን ሊገናኙ ይችላሉ።

zegfanta@outlook.com